በስደት ላይ ያለው ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት

THE LEGITIMATE HOLY SYNOD OF THE
ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH
PATRIARCHATE HEAD OFFICE IN EXILE

ቀን፡ 11/006/07 ዓ.ም.
Date: 02/18/2015
ቁጥር: ጠቤክ/0107/07
Ref. No: 0107/15

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐ3:16

ለ የብዙኃን መገናኛ/ሚድያ ክፍል፤

"የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን።" 2ቆሮ13:14

ጉዳዩ፤ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ መርቆሬዎስን 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመትና በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ሜሪላንድ የተገዛውን የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የምረቃ በዓል ፕሮግራምን ይመለከታል፤

በሕጋዊው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በዓለም ላይ ለምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መስፋፋት እንዲሁም ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ሰላም፤ አንድነትና ፍቅር ቅድሚያ በመስጠት ለትውልድ የሚተላለፉና በታሪክ የሚመዘገቡ በርካታ ቋሚ ሥራዎችን ለመሥራት የቻለው በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት፤በእርስዎና እርስዎን በመሳሰሉ በጎ ኅሊናና ቅን አመለካከት በአላቸው ምእመናን ያልቋረጠ ድጋፍና ጸሎት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው።

ስለዚህ ቅዱስነታቸው ለታላቁ የቤተ ክርስቲያን መዐርግ የበቁበትን 25ኛ ዓመት በዓለ ሢመት ምክንያት በማድረግ ቅዱስ ሲኖዶስ በቅርቡ የገዛውን አዲስ የመንበረ ፓትርያርክ ሕንጻ ለማስመረቅ በታላቅ መንፈሳዊ ዝግጅት ላይ ይገኛል። ይህ ታላቅና ታሪካዊ ፕሮግራም ቅዳሜ ሚያዝያ 24 ቀን 2007 ዓ.ም (Saturday, May 2,2015) The Catholic University of America, 620 Michigan Ave., N.E., Washington, DC 20064 የሚከበር መሆኑን በመገናኛ ብዙኃን በመላው ዓለም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዲያስተላልፉልን በልዑል እግዚአብሔር ስም በአክብሮት እንጠይቃለን።

"ከመንፈሳዊ አክብሮት ሰላምታ ጋር"

ቆሞስ አባ ጽጌድንግል ደገፋው
የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ
Komos Abba Tsigedengel Degefaw
General Manager of the Patriarchate Head Office

ግልባጭ፤

ለቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጽ/ቤት፤
ለመንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፤
ለቋሚ ሲኖዶስ አባላት በያሉበት፤